እርሱ ውሃው አፅጂ ነው፤ ውስጡ የሞተም ሐላል ነው።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ «አንድ ሰው የአላህን
መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ በማለት ጠየቀ "የአላህ መልክተኛ ሆይ!
እኛ በባህር እንሳፈራለን፣ ከኛ ጋርም የተወሰነ ውሃ እንሰንቃለን። በዚህ በያዝነው ውሃ ዉዱእ ብናደርግበት እንጠማለንና በባህር
ውሃ ዉዱእ እናድርግን?" የአላህ መልክተኛም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ
በማለት መለሱ: "እርሱ ውሃው አፅጂ ነው፤ ውስጡ የሞተም ሐላል ነው።"»
[رواه أبو داود والترمذي والنسائي وابن ماجه وأحمد] [ነው። ሶሒሕ[

አንድ ሰውዬ ነቢዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ በማለት ጠየቀ "እኛ ለማደን ወይም ለንግድና ለመሳሰሉት በባህር ላይ ጀልባዎችን እንሳፈራለን። ለመጠጥ የሚሆን ትንሽ ውሃንም ከኛ ጋር እንጭናለን። የመጠጡን ውሃ ለዉዱእና ለገላ ትጥበት ከተገለገልን ያልቅብንና የምንጠጣውን አናገኝም። ታዲያ በባህር ውሃ ዉዱእ ማድረግ ለኛ ይፈቀድልናል እንዴ?" ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ስለባህሩ ውሃ እንዲህ አሉ "ውሃው ንፁህም አፅጂም ነው። በርሱም ዉዱእ ማድረግ፣ ገላ መታጠብ ይፈቀዳል። ከርሱ የሚወጡን አሳዎችንና ሌሎች የባህር እንስሳዎችንም ሙተው ሳይታደኑ ከላይ ተንጣለው ቢገኙ ራሱ መብላት ይፈቀዳል።"

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/8355